Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

የሰበር መ.ቁ. 20727

ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

.. አሰግድ ጋሻው

ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

.. ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- አቶ ገረመውሸዋ አጥሌ ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የኢት/ያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ ወ/ሮ ታሪኳ ላዕከ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌ.ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች በመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ሚች ልጂ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለ እኔም አባቱ በመሆኔ የወራሽነት ማስረጃ አግኝቻለሁ በዚሁ የወራሽነት ማስረጃ መሠረት በመልስ ሰጭ በኢት/ያ ንግድ ባንክ በሚች ልጂ ስም በተከፈተው የሂሣብ ቁጥር የሚገኘው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለኝ ብጠይቅ መልስ ሰጭ ከልማዳዊ አሠራሩ አፈንግጦ ክፍያ ከልክሎኛል ስለሆነም ክፍያ ይፈቀድልኝ ዘንድ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም ለክሱ መልስ ሰጥቷል ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ጉዳይ ተመልክቶ ከሣሽ የአሁን አመልካች ለክሣቸው ማስረጃ አድርገው ያቀረቡት በሥ/ፋ/መ/ቁ. 1102/93 በሰኔ 18 ቀን 1993 ዓ.ም በፍ/ቤት የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ማስረጃ አመልካች የሚች የአቶ ዓለምን ግዛው ገረመው ወራሽ

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

መሆናቸውን የሚያሣይ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 947 እና ተከታዩቹ መሠረት የውርስ ሀብት ተጣርቶ የወራሽ ድርሻ ተለይቶ የተሰጠ ማረጋገጫ አይደለም በመሆኑም በዚህ የወራሽነት ማስረጃ ብቻ ክፍያ እንዲፈፀም ለመጠየቅ የማይችሉ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የፌ.ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታውም የቀረበውም፡

- በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 947 መሠረት ወራሹ እራሱ አጣሪ መሆኑን
- ባንክ እኔን ለመሞገት አይችልም፤ ጉደዩ አይመለከተውም፡፡
- ጥርጣሬ ካለውም ጣልቃ ማስገባት የሚችል መሆኑ ከግምት ውስጥ ላይገባ የተሰጠው ብይን ሕጋዊ መሠረት የለውም ይታረምልኝ በማለት ነው፡፡ መልስ ሰጭም በበኩሉ የሟች ንብረት እስካልተከፋፈለ ድረስ የተለዩና የማይከፋፈል ሆኖ የሚቆይ ስለሆነ፡፡
- የውርስ ሁከቱም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.946 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መጣራት ያለበት በመሆኑ ፡
- የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘት ብቻ ሣይሆን ሌሎች ወራሾች ክሱ ማጣራት እንደሚገባ የውርስን አከፋፈል ሁኔታ ማሣወቅ ስለሚገባ ይህ ሁሉ ተጣርቶ የወራሽ ድርሻ በፍ/ቤት ሊወሰን ይገባል እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 896 እንደተመለከተው ባንክ ክፍያ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ለአስቀማጩ፣ ለወኪሉ ወይም መብት ላገኙ ሰዎች ብቻ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ አይመለከተውም መባሌ አግባብነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

በወራሽነት አቋም ንብረት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅ ወገን ወራሽ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ማግኘት ብቻ ሣየሆን የውርሱንም ድርሻ ልክ የያዘ ማስረጃ ማግኘት እንደሚገባው እና ፍ/ቤትም ገንዘብ ጠያቂው የወራሽነት ሰርቲፍኬት በሚሰጥበት ጊዜ ወራሽነቱ እና የሚወረሰውን ሀበት ዓይነትና ክርክር በመጠን በመለየትና ከውርሱም የወራሾች ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ ለይቶ ይህንኑ ሁሉ ካረጋገጠ በኋላ ማስረጃውን መስጠት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 ተደንግጓል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ከላይ የተመለከተውን ሂደት ተከትሎ ሕጉ በሚያዘው መሠረት በእርግጥም ብቸኛ ወራሽ እራሣቸው ብቻ ስለመሆናቸው ተጣርቶ እና የውርስ ድርሻቸውም ልክ ምን ያህል እንደሆነ ተለይቶ የተሰጠ መሆኑን አያመለክትም፡፡

መልስ ሰጭም የሚከራከረው በወራሽነት ማስረጃው ብቻ ክፍያ ብፈጽም ከክፍያ በኋላ ሕጋዊ ወራሽ ሊመጣ እና የክፍያ ጥያቄ ሊያቀርብ በሕጋዊ የወራሽነት የመስክር ወረቀት መሠረት የተደረገ ክፍያ በመሆኑ ኃላፊነት ሊያስከትልብኝ ይገባል የሚለውን መሠረት አድርጎ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢ እና ተቀባይነት ያለው ነው፡፡

ሆኖም በዚህ ጉዳይ አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ያገኙት በ1993 ዓ.ም ነው ከዚያም በኋላ እኔም ልወርስ ይገባል በማለት የቀረበ ወገን የለም የቀረበው ማስረጃም የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ የውርስ ድርሻቸውን አለማመልከቱ እንጂ አባት በመሆናቸው ምክንያት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው ይህም ማስረጃ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ውድቅ አልተደረገም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ በባንኩ ለተቀመጠው ገንዘብ ሙሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ባያስረዳም በማስረጃው መሠረት በአባትነታቸው ማግኘት የሚገባቸውን ልክ የማግኘት መብት የሚሰጣቸው ስለሆነ በሚች ስም በባንክ ተቀምጦ ከሚገኘው ገንዘብ ግማሹ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete Documents

ው ሣ ኔ

1. በሚች ዓለምን ግዛው ገረመው ስም በመልስ ሰጭ /በኢት/ያ ንግድ ባንክ ተቀምጦ ከሚገኘው ገንዘብ ግማሹ ለአመልካች ለአቶ ገረመውሸዋ አጥሌ ወጭ ሆኖ ይከፈል ብለናል።
2. በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 41033 ሐምሌ 09 ቀን 1996 ዓ.ም በፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33399 ግንቦት 05 ቀን 1997 ዓ.ም እንደቅደም ተከተሉ የተሰጠው ብይን እና ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 346/1/ መሠረት ተሽሯል።

የማይነበብ የአምስት ደኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ